ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ
Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity
Efdpu@aol.com www.Finote.org

በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ
ግንቦት 3 ቀን 2008 ዓ.ም. የተላለፈ

# ምን ዓይነት ሀገር እንፈልጋለን ?

ማነኛውም ሕዝብ ፤ የሚኖርባት ሀገሩ ፤ የታፈረች፤ የተከበረች፤ የበለፀገችና፤ የተመቸች እንድትሆንለት ይመኛል፡፡ የራሷን ነፃነት ጠብቃና አክብራ፤ የዜጎቿንም ነፃነትና መብት ፤ አስከብራ የምትገኝ ሀገር ይሻል ። ዕድገትና ብልፅግና፤ ምቾትና ደስታ የሚያገኝባት ሀገር እንድትኖረው ያልማል ። ኅልሙን ፤ ወደ ኅልው ለመለወጥ ግን ፤ ታላቅ ተግባር ማከናወን እንዳለበት ይጠበቅበታል ። በአጭሩ ፤ ሁሉም ሕዝብ ፤ በሚኖርባት ሀገሩ፤ የተሟላ ነፃነትና ሠላም፤ የተረጋጋ ኑሮና የደህንነት ዋስትና እንዲረጋገጥለት ይፈልጋል። ይኽንን ፍላጎትና ምኞት በተጨባጭ ድርጊት ካላስማሰከረ፤ ምኞቱና ተስፋው፤ ብርቅርቅ ከመሆን ያለፈ ዕርባና አያስገኝለትም ።

በስንፍና የጠነከረ፤ በቀረርቶ ያባረረ በዳንኪራ ያስፈራራ፤ በፉከራ የተፈራ ፤ በምፅዋዕት የከበረ፤ በልመና የበለፀገ ኅብረተ ሰብ መኖሩን በታሪክ ተመዝግቦ አልቆየንም ። ሀገርን የማዳኑ፤ ሕዝብን ነፃ የማውጣቱ፤ ጠላትን የማቸነፉ ታላቅ ሥራ፤ ማስብንና ብዙ ውጣ ወረድ ብቻ ሳይሆን፤ ከባድ መሥዋዕትንም የሚያስከፍል እንደሆነ ሁሉም ሊረዳው ይገባል ።

ታሪካዊ ሀገራችን፤ አኩሪ ታሪኳ፤ ተከብሮ እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ ለዜጎቿ የምትሆን ፤የምትመች ሀገር መሆን አለባት። ይህ ማለት ግን ፤ አንዳንዶቹ እንደሚሉት፤ " ለኛ ካልሆነችና ካልተመቸች፤ አንፈልጋትም" ማለት አይደለም ። ከፍቶንም ይሁን ተመችቶን፤ የምንፈልጋትን ሀገር ፤ ምን ዓይት ሀገር መሆን እንዳለባት አምነን ፤ ገንብተንና አሳምረን እርሷ እየኖረች እኛም በሠላም የምንኖርባት ሀገር እንድትሆን እንመኛለን ።ይህ ደግሞ ፤ የማንነታችንና የኅልውናችን አልፋ-ዖሜጋ ነው ። የትግላችንም መነሻና- መድረሻ ዐብነቱ ይኸው ነው ።

ይህንን ከተገነዘብን፤ የነገይቱ ኢትዮጵያ ፤ምን ዓይነት ሀገር እንድትሆንልን እንፈልጋልን ? ለሚለው መሪ ጥይቄ ትክክለኛውን መልስ አግኝተን ፤ ለምንፈልጋት ሀገር ኅላዊ በርትተን- ተባብረን መስራት ካልቻልን፤ ፍፃሚያችን እንደ ባቢሎን ግንብ ሰሪዎች እንዳይሆን እንሰጋለን። ይኽ ስጋት ደግሞ ከባዶ ሜዳ የመጣ አይደለም። ከተጨባጩ የሀገራችን ጊዚያዊ ሁኔታ የመነጨ እንጅ !

ከነገረ-ቀደም ፤ የዛሪይቱ ኢትዮጵያ ምን ዓይነት ምድር ሆናለች? ብሎ መጠየቅ፤ ሊኖርብን ነው ። የጥያቄው አቅጣጫ ማተኮር የሚገባው ደግሞ፤ በማንነት ዙሪያ ሳይሆን፤ በኅልውና መሠረት ላይ መሆን ይኖርበታል ። ሀገራችን የማንነት ችግር የለባትም። ኖሯትም አይውቅ። ማንነቷ፤ በታሪክ ያስመሰከረች፤ ድፍን ዓለም ያወቃት- ፀሀይ የሞቃት ሀገር ነች ። በዚህም ዜጎቿ ይኮራሉ። ፀላዒዎቿ ግን ያፍራሉ ። **ኢትዮጵያ** የሚለውን ቃል ሲሰሙ የሚርበተበቱትም በዚህ ምክንያት ነው ።

በማንነትና በኅልውና መካከል በሚገኝ ውዥንብርና ብዥታ ውስጥ ሆኖ መገኘት፤ ምን ዓይነት ሀገር እንድትኖረን እንፈልጋለን ? የሚለውን ጥያቄ በትክክል ለመመለስ የሚያስቸግር ይመስለናል ። በመሠረቱ ዛሬ ፤ የሀገራችን ሕዝብ ጥያቄ፤ የማንነት ሳይሆን ፤ የኅልውና ጉዳይ መሆኑን ሁሉ ይስማማበታል

የወቅቱ ጥያቄ ያተኮረው፤ በሀገር መኖር- አለመኖር ፤ በሕዝቦቿ አብሮ መቀጠል አለመቀጠል ላይ ነው።፤ ተተኪው ትውልድ፤ አብሮ የሚኖርባት ሀገር፤ ትኖረዋለች- አትኖረውም ? ይህችንስ ሀገር ፤ ለሚቀጥለው ትውልድ የሚያስረክበው ማን ነው ? ለማንስ ያስረክባታል ? ኽረ ለመሆኑ፤ አስረካቢና ተረካቢስ አለ ወይ ? ወደፊትስ ይኖራል ? ይህ ነው ዛሬ የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚያስጨንቀው፤ የሚያብሰለስለው ! የማንነት ችግር ሳይሆን፤ የህልውና ጉዳይ ነው። የመኖር

አለመኖር ጉድይ በኢትዮጵያ አግማስ ላይ ማንዣበብ ከጀመረ ቆይቷል ። እነኝህን ጥያቄዎች ለማንሳት የሚያስገድዱ **መሠርታዊ ምክንያቶች አሉ።**

1ኛ. ኢትዮጵያን፤ በዕቅድ የሚያጠፋ፤ ሕዝብን በዘርና ጎሳ የሚከፋፍል መርዝኛ ሥርዓት ተሰይሟል። ለዚህ እንዲመቸውም የራሱን " ህገ መንግሥት አንቀፅ 39ን " ቀርጾ፤ የደደቢቱን ፀረ ኢትዮጵያ ሴራ ህግ አድርጎ፤ ሀገር ለመበታተን አመቻችቷል። "ብቃትም" አግኝቷል ።

በማዕከላዊ መንግሥት ሥልጣን ማካበትና መጠቀም አኳያ ሲታይ፤ ይህ አገዛዝ እጅግ ሲበዛ፤ አምባገነንና ፍጹም ቶታሊትርያን ሥር ዓት ነው። ከዚህ አኳያ ሲገመገም፤ ምናልባትም፤ ከዚህ ዘረኛ ሥር ዓት በፊት ከነበሩት ሁለት አገዛዞች፤ በዘረኛነቱ አይነተኛ ከመሆኑም በላይ፣ በአንፃራዊነት፤ አምባገነንነቱ፤ ሁሉ-አቀፍ ነው ቢባል ስህተት አይሆንም። እንደ ቻይና ሁሉንም ስልጣን መዳፉ ስር ያስገባ ነው ። መቶ በመቶ/ 100% በምርጫ አቸንፌአለሁ ብሎ ራሱን የሚያታልል ጉደኛ ቡድን መሆኑን አስመስክሯል ። መቶ በመቶ 100 % አቸንፌአለሁ የሚል አገዛዝ በዓለም የመጀመሪያውን ክብረ-ወሰን ያገኘ፤ ሀፍረተ-ቢስ ቡድን ዛሬ ፤ በሀገራችን ተንሰራፍቷል።

የሀገሪቱን የፖለቲካ፤ የምጣኔ ሃብት፤ የንግድና- ገበያ፤ የባንክና ሌሎቹን የሀብት ምንጮች ሁሉ ተቆጣጥሮ ፤ያለአንዳች ስጋት፤ የፈለገውን ይፈፅማል ። ይህንን ገደብ-የለሽ ሥልጣኑን በመጠቀም፤ ሀገር የማፈራረሱን ተግባር እየፈፀመ ይገኛል ። ለዕቅዱ ማስፈፀሚያ ኃይል የሚሆነውን፤ ከአንድ ብሄር የተገነባውን የጦር ሠራዊት መስርቷል። ሀገር ለመበታተን ከዚህ የበለጠ ምን ኃይል ሊኖር ይችላል?

በአንፃሩ ግን ፤ሀገሪቱን ከመፈራረስ ሊያድናት የሚችል፤ በቂና አስተማማኝ ኃይል በአሁኑ ሰዓት የለም ይባላል ! በተመልካችም በኩል ፤ ተቃዋሚው፤ የወረቀት- ነብር ከመሆን ያለፈ ተግባር እንዳላሳየ ተገምቷል ። ይህ ግምት ግን፤ ለትግሉ አይጠቅምም ። "ባለቤቱ ያቀለለውን ዐሞሌ፤ ባለዕዳ አይቀበለውም " ነውና ጠላት፤ የልብ ልብ እንዳይሰማው ፤ አፍራሽ ንግግርና ተግባር ከመፈፀም ሁሉም ሊያስብበት ይገባል ።

2ኛ. ሀገራዊ ብኄረተኝነት ( Ethiopian Nationalism ) እየመነመነ፤ የጎሳና የክልል ብኄረተኝነት (Regional Loyalty ) እየነገሠ በመሄድ ላይ ይገኛል። የአብሮነቱ እሴትና መንፈስ እየደከመ በመሄድ ላይ ይታያል። ተለያይቶ ለመበታተን የሚያመቸው ጥርጊያ መንገድ እየተጠረገለት ነው። ለዚህም የህግ ድጋፍና ማስፈጸሚያው ተስተካክሎለታል ። ለሀገሪቱ ሉዓላዊነትና ለሕዝቧም አንድነት የሚናገሩ፤ የሚጽፉና የሚታገሉ ጋዜጠኞች፤ ደራሲያን ሀገር ወዳዶችና የድርጅት መሪዎች ፤ ወኅኒ ቤት ወርደዋል። ሌሎቹም ድብዛቸው ጠፍቷል። ሕዝብና ሀገር በአንድነት በመጥፋት ላይ ይገኛሉ።

ሀገርን ሀገር ሊያሰኛው የሚችል ዋነኛው መሠረት፤ ሕዝብ ነው ። ሕዝብ እየጠፋ በመሄድ ላይ መሆኑን እያየ፤ ኢትዮጵያ፤ ዘለዓላማዊት ነች ብሎ የሚፅናና ካለ፤ የዓለምን ታሪክ መዝገብ ሊያገላብትጥ ይጠበቅበታል ። ታሪክን ከተገነዘበ ፤ እራሱን እያታለለ፤ ሌላውንም እንዳያታልል ይረደዋል ።

ባቢሎናዊያን፤ ሞንጎላዊያን፤ አሦራውያን፤ ገለዳውያንና፤ ሌሎች ጥንታውያን ሕዝቦች ፤ የት ደረሱ ? የት ገቡ? ምን በላቸው? ብሎ መጠየቅ ይገባል ። የወቅቱ ትዉልድ፤ ይህንን ጥያቄ እየጠየቀ፤ ተጨባጩን ሁኔታ እየተገነዘበ፤ ሀገሩ ወደ የት አቅጣጫ እንደምትሄድ አውቆ ፤ መከላካያ ካላበጀ፤ ነግ- ተነገ-ወዲያ፤ የጋራ ሀገር ትኖረኛለች ብሎ ራሱን ሊያታልል አይገባውም ።

የውስጥና የውጭ ባላንጣዎች ተባብረው፤ ኢትዮጵያን እየገዘገዟት እንደሆነ መረዳት ፤ ነገ፤ ወየው ! ወየው ! ከማለት ያድናል። ውሃ እየሳሳቀ እንደሚወስድ ሁሉ፤ ሀገርና ሕዝብም ቀስ በቀስ፤ በስልት እየጠፉ መሆናችውን መረዳት ብልኅነት ነው ። ከምዕራባዊያን አስከ መካከለኛው ምስራቅ ላሉ የኢትዮጵያ ባላንጣዎች በማኀብደዱ ቀንቶት የስልጣን ኮርቻ ላይ የተሰየመው የዘረኞች መንጋ " ደርግን ያሸነፍነው ፤ በጦር ሜዳ ብቻ ሳይሆን፤ የጭንቅላት ብልጫም (Intelligence )

አሳይተን ነው።" ያለውን ባዶ ጉራ ፤ ማሳፈር የሚቻለው፤ ሀገር የማጥፋት ዕኩይ ተግባራቸውን በመደምሰስ ብቻ ነው። ይዋል ይደር እንጅ፤ ይህ መፈፀሙ ደግሞ አይቀርም ። ያም መፈፀሙ እንዳለ ሆኑ ግን፤

" ከፍት ይዋል ፤ ከፍት ይደር ብለው ሲመርቁ፤

ቤታችን ከፍት ሆነ ሰዎቹም አለቁ ። "

እያሉ ማንጎራጎር ፤ ኢያጽናናም !

3ኛ. የሀገሪቱ የተፈጥሮ ድንበሯ ፤ ዓለም አቀፍ ወሰኗ ፤ የት ላይ እንደሆነ ለይቶ ከማይታወቅበት ደርጃ ተደርሷል። በብዙ መቶዎች ኪሎ ሜትር የሚከነዳው የሀገሪቱ ምዕራባዊ ግዛት ወድ ሱዳን ግዛት ተጠቃሏል። በዚህ ምክንያት፤ የኢትዮጵያ የቆዳ ስፋት ተጨማትሯል። ይህ ደግሞ፤ የስፋትና ጥበት ጉዳይ ሳይሆን ፤ የኀልውናዋ ዓይነተኛ ጥያቄም ጭምር ሆኗል ።

4ኛ. ባዕዳን፤ የሀገሪቱን ሉዓላዊነት እየጣሱ በመግባት፤ በጠረፍ አካባቢ የሚኖሩትን ዜጎቻችንን፤ ሴት -ወንድ፤ ህጻን ሽማግሌ ሳይለዩ ገድለው ይሄዳሉ። የሀገራችንን ጠረፍ መድፈራቸው አልበቃ ብሏቸው፤ ሠላማዊ ኢትዮጵያውያንን ፤ እየገደሉ ሲሄዱ፤ መንግሥትና ሀገር አሉ ብሎ ማለት እንዴት ይቻላል ? ከጥቂት ቀናት በፊት ፤ በጋምቤላ አካባቢ ከሁለት መቶ በላይ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በግፍ ተጨፍጭፈዋል ። ከዚህ ቁጥር ያለነሱ ዜጎች ታፍነው ተወስደዋል ።

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ ከመኖር ፤ የሰማይ አሞራ ይብላኝ ፤ የዱር አራዊት ይፍጀኝ ፤ አሣ ነበሪ ይዋጠኝ እያለ በመሰደድ ላይ ያለው ዜጋ በየቦታው የሚያጋጥመው የሕይወት አደጋ አልበቃ ብሎ፤ በገዛ ሀገሩ የሚኖረውንም ሳይቀር ከወጭ የሚመጡ ባዕዳን እየገቡ ገድለውት ይሄዳሉ። ለሰሚው ግራ ሆኗል፡፤ ለዚህ ወንጀል የመጀመሪያው ተጠያቂ ማን ሊሆን ይችላል? የሀገሩን ዜጎች ከውጭ ጥቃት የማያድን መንግሥት ፤ እንዴትስ የኢትዮጵያ መንግሥት ነው ሊባል ይችላል ? ለመሆኑ፤ የኢትዮጵያን ጥቅም ሊያስጠብቅ የሚችል ኢትዮጵያዊ መንግሥት አለ? የለም ? ብሎ መጠይቅ የተጀመርው መች ነው ? ሰለሆነም ነው ገና ከጠዋቱ ወያኔን "የኢሕአዴግ መንግስት" እያሉ ከሚጠሩት ሃሳዊ ምስክሮች በሚለየነው የአንድነት ሃይል የወያኔ አገዛዝ እንጅ መንግስት ሊባል አይችልም የሚባለው።

ኪራይ ሰብሳቢ ? ወይስ ለሀገር አሳቢ ? ሀብት ዘረፊ ? ወይስ ጠረፍ ጠባቂ ? የሀገር ቀናዒ ? ወይስ የባዕዳንን ጥቅም አስከባሪ ? ሀገር ቆራሽ ? ወይስ የሄደን አስመላሽ ? ታሪክ ወዳጅ ? ወይስ ሀገር አዋራጅ ? ጥያቄዎቹ ተዘርዝረው አያልቁም።

የአሁኑ ትውልድ፤ ምን ዓይነት ሀገር እንዲኖረው ይፈልጋል ? ይህንን ጥያቄ መመለስ ያለበት እርሱ ራሱ ነው። ማንም ሊመልስለት አይችልም ። ራሱ የጠየቀውን ፤ ራሱ መመልስ እንዳለበት ማንም ሊነግረው አይገባም ። ልትኖረው የሚፈልጋትን ሀገር፤ ምን ዓይነት ሀገር እንድትሆን ከፈለገ ፤ የምንንም ፈቃድ ሳይጠይቅ ፤ ያችን የሚፈልጋትን ሀገር፤ ራሱ ታግሎ ማግኘት አለበት ።

ይህንን የሚያድረግ ትውልድ እየተፈጠረ መሆኑ ተስፋ ሰጭ ሆኗል ። ኢትዮጵያ ሀገራችን የወላድ መካን ሆና አልቀረችም ። ጀግና ወላጅ እናቶች በድባብ ይኽዱ!

ያ አሳረኛና መሥዋዕታዊ ትውልድም በበኩሉ ፤ የራሱን ፤ ድርሻ ተወጥቷል ቢባልም፤ መልስ ለመመልስ ግን አይገደድም አይባልም። ይገደዳል ! እየጠየቀ ይጠየቃል ! መልስ ለማግኘት ግዴታ እንዳለበት ያምናል ። የራሱን ድርሻ ፤ መወጣት አለመወጣቱን ፤ ኀብረተስቡ እንዲረዳለት ግን ይጠይቃል ! የጀመረውን እስኪፈፅም ድረስ ግን መልስ ከማግኘት ነፃ ሊሆን አይችልም። ድርብ ድርብርብ ኃላፊነቶች እንዳሉበት ይገነዘባል ። በአንድ በኩል፤ ለሕዝብ የገባውን አደራና ቃል-ኪዳን ጠብቆ የጀመረውን ትግል መቀጠል ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ፤ አኩሪ የትግል ታሪኩንና የተከፈለውን መሥዋዕት በቀናዒነት የመጠበቅ፤ የማክበርና የመከላከል ኃልፊነት እንዳለበት በአፅንኦት ይረዳል ። ነገ ልትኖረው የሚፈልጋትንም ሀገር የሚያያት፤ ካለፈው ታሪኩ በመነሳት ፤አሁን ያለበትን ሁኔታ በመገንዘብና የነገዋን ኢትዮጵያ በራዕዩ እያስገባ ነው ።

አብዛኛዎቹ የዓለም ሀገሮች፤ ጎልማቸውን ተጨባጭ ከማድረጋቸው በፊት፤ ምን ዓይነት ሀገር እንደሚፈልጉ አስቅድመው አውቀው ይተልሚታል ። የሚኖሩባት ሀገር ምን ዓይነት ሀገር መሆን እንዳለባት አስበውና አቅደው ፤ ይፈጥሯታል። ያሳድጓታል ። ያበጇታል። ይገነቧታል። ለነፃንቷም ይታደጓታል። ለራሳቸው ምቾትና ብልፅግና፤ ዕድገትና ርምጃ ያመቻቿታል። ለራሳቸው ብቻ ሳይሆን፤ ለሚቀጥለው ተተኪ ትውልድ እንደትጠቅም፤ አመቻችተው አሳድገውና ነፃነቷን አሰረግጠው ያስረክባሉ። ካለው ላይ እየገነቡ ይሄዳሉ እንጅ፤ ያለውን አያፈርሱም። ሀገር አይሸጡም። ከተመቻቸው ግን ሌላ ገዝተው ካለው ላይ ይጨምራሉ። ይህ ደግሞ በዓለም በሚገኙ ሀገሮችና ሕዝቦች የተረጋገጠ ነው።

ተረካቢው ፤ የወቅቱ የሀገራችን ትውልድ ግን ይህንን እድል አላገኘም። ደርግ የሰነጣጠቃትን ሀገር፤ ወያኔዎቹ እንዲያፈራርሷት ሆና ጠበቀቻቸው። ጭራሽ ለመፈራረሷ ምክንያት አገኙ። አጥብታ ያሳደገቻቸውን ሀገር መቅኖ እያሳጧት ነው።

አሁን እኮ፤ የትኛዋን ሀገር ነው ምን ዓይነት ሀገር እንድትሆን የሚፈለገው ሳይሆን፤ እረ ለመሆኑ፤ የሀገሪቱ ቆዳ ስፋትም ሆነ ሕዝቧ ፤ ጎልውናቸው ጠብቀው እየቆዩ ናቸው ወይ? ለሚለው ጥያቄ፤ መልስ ማግኘት አለመቻሉ ነው። ምን ዓይነት ሀገር እንዲኖረን ከመመኘታችን አስቀድሞ፤ የሀገሪቱን ጎልውና ማስቀድም ከሁሉ በላይ፤ ከማንኛውም በፊት ቅድሚያ ሊሰጠው እንደሚገባ ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሠረታዊ ጥያቄና የመጀመሪያ ሀገራዊ አጀንዳ ከሆነ ቆይቷል ።

ይህ ጥያቄ በአስተማማኝ መልኩ እስካልተመለሰ ድረስ፤ ለመንግሥት ሥልጣን፤ ለፖለቲካ የበላይነት፤ ለፓርላማ ወንበር፤ ሀብት -ንብረት ለማካበት፤ መመኘት፤ ከንቱ፤ የከንቱ ከንቱ ሆኖ መቅረት ይመስለናል ። ሀገር ሳይኖር፤ ለፖለቲካ ሥልጣን መመኘት፤ የከልታማዋን ገበሬ ሚስት ምኞት እንደመመኘት ይቆጠራል ።

የሴትዮዋ ታሪክ፤ ይኸንን ይመስል ነበር ።

" አክርማ ቆርጨ፤ ሌማት ሰፍቸ፤ ሌማቱን ለንጉሥ አበርክቸ፤ ንጉሡ ላም ሰጥተውኝ፤ ለሜ ጥጃ ወልዳልኝ፤ ጥጃዋን እቤት ውስጥ አስራታለሁ። " ብላ ለባሏ ታማክረዋለች ። ባሏም፤ " ጥጃዋን እቤት ወስጥ አታስሪም ። " ይላታል። አስራለሁ ። አታስሪም። በሚል ክርክር፤ ጠብ የፈጠራል ። ባል ሚስቱን፤ በቆመጥ ጭንቅላቷን ብሎ ይገድላታል ። ምኞቷ ብቻ ሳይሆን ፤ ሕይወቷም መና ሆኖ ቀረ።

ምን ዓይነት ሀገር እንዲኖረን ስምምነት ማድረግ ፤ የቅድሚይ- ቅድሚያ፤ መጀመሪያና- መጨረሻ፤ ሊሆን ይገባል ብለን እናምናለን !

ኢትዮጵያ ዘለዓለማዊነት ነች !